# …መገኘት አለበታ!



በማለዳ፣ በማታ፣
በቃሊቲ፣ ሰበታ፣
የሰማኋት ኮሽታ
ምንጯ…
        መገኘት አለባታ!

በግድም፣ በውዴታ
በረብሻም፣ በጸጥታ
የተሰማው ውካታ
ምንጩ…
        መገኘት አለበታ!



በሃድያ፣ ከምባታ
በአምቦ፣ በሆለታ
የወደቀች ጠብታ
ምንጯ…
        መገኘት አለባታ!



በመቀሌ፣ በእንደርታ
የተወራው ሹክሹክታ
ባውጫጭን፣ በአፍርሳታ
ምንጩ…
        መገኘት አለበታ!

ከአልጋ፣ ከመኝታ
አግድም ተመቻችታ
ያመለጣት ጨዋታ
ምንጩ…
        መገኘት አለበታ!



በቁልቢ፣ በባታ
ሐረር፣ ጋራ-ሙለታ
የሸረቡት፣ ዱለታ
ፍቺው…
        መገኘት አለበታ!

ያራዳ ጋለሞታ
ለድሆቹ መጽውታ
ያስነሳችው ጫጫታ
ምንጩ…
        መገኘት አለበታ!



በአርማጭሆ፣ ገንደፍታ
በዶርዜ፣ በወላይታ
ሐሜትና፣ ፉተታ
ምንጩ…
        መታወቅ አለበታ!





በሐሰት አሉባልታ
የተኮሱት እሩምታ
የተሳበውም ቃታ
ቁጥሩ…
        መታወቅ አለበታ



የአቋማቸው ገጽታ
የልባቸው ትርታ
በምርመራ እስኪፈታ
ውስጡ…
        መገኘት አለበታ!



ሳናበዛ ሐተታ
ጉዳዩም ሳይምታታ
ነገሩ እንዲገታ
ከዚህ…
        መዘጋት አለበታ!

ገ/ኢ. ጐርፉ።